# <u>የከረረ ይበጠሳልና ....</u>

<u>ብርሃኑ (ከአዲስ አበባ)</u>

በተወለድኩበት ከተማ ያሳለፍኩት የልጅነት ሕይወት የሃይማኖት ልዩነት አንድ ቀንም ቢሆን በመሃከላችን የነበረው ወንድማዊ ትስስር ከማጠናከር ገድቦን አያውቅም። የሌላ እምነት ተከታይ የሆኑት ጎረቤቶቻችን ቤት ገብቶ ከታላቅ እህቴ ጋር አብሮ መብላትና መጠጣት ልማዳችን ነበር። እነዚያም የጎረቤት ወንድም እህቶቻችን ወደ እኛ ቤት መጥተው ተመሳሳይ ተግባር ይፈጽማሉ። ልዩነት ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ላይ ነው - በእኛም ሆነ በጎረቤቶቻችን ቤት የተሰራው ምግብ ሥጋ ካለው ***የምንበላው መረቅ መረቁን ብቻ ነበር።***

በዚህች ከተማ የተጠነሰሰው የአብሮነት ስሜትና ፍቅር ዛሬ ድረስ ዘልቆ ቤተሰባዊ በሚባል መልኩ ወዳጅነታችን ጠንክሮ በደጉም በክፉውም ጊዜ እየተጠያየቅን በመኖር ላይ ነን። በየራሳችን የእምነት በዓላትም የ ''እንኳን አደረሰን!'' የመልካም መልዕክቶች እየተለዋወጥን እዚህ ደርሰናል፤ እንቀጥላለንም።

በአንድ የሕይወቴ ምዕራፍ ደግሞ ለሃይማኖት እምብዛም ዋጋ በማይሰጥ የአገሪቱ ክፍል ኖሬያለሁ። በዚህ ሥፍራ የሚኖሩት ወገኖች በተለይ ለአመጋገባቸው እምብዛም የማይጨነቁ ከመሆናቸው ውጭ፤ የሌሎች ወገኖችን ሃይማኖት ድርድር ሳይገቡ የሚያከብሩና በእነሱም የእምነት ጉዳይ ሌሎች ጣልቃ እንዳይገቡባቸው የማይፈልጉ ናቸው። የሚፈልጉትን እምነት ዋጋ ሰጥተው በተቀበሉ ጊዜ ደግሞ ምርጫቸውን አስከብረው ተገቢውን ያደርጋሉ። ከዚያ ውጭ ባለማመንም ይኖራሉ። እምነታቸው ነውና።

መርካቶ ውስጥ በአጋጣሚ ያወቅኳቸው የሁለት እምነቶች ተከታዮች አንዳቸው ሌላቸውን የሚጠሩበት ማሞካሻ ፍቅራቸውን ገላጭ ሆኖ ይሰማኛል። የእስልምና እምነት ተከታዩ ክርስቲያንና ጓደኛቸውን ሲጠሩ ከስማቸው አስከትለው ታቦት አስከትለው ነው። እኔ ለጊዜው እኔ ረሳሁት እንጂ የክርስትና እምነት ተከታዩ ጓደኛቸውን የሚጠሩት በሌላ ማሞካሻ አውቃለሁ።ጓደኛሞቹ በዚህ መልኩ የሚጠራሩት ለረጅም ዘመናት በቆየው ወዳጅነታቸውና አንዳቸው ለሌላቸው እምነት ባላቸው አክብሮት መሆኑንም ተገንዝቤያለሁ።

ይህንንና ይህን መሰል የሃይማኖት ልዩነት ያልበገራቸው የእምነት መገለጫዎች በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫዎች ያጋጥማሉ። ሆኖም በመቻቻልና በመከባበር መንፈስ አብሮ መኖራችን ዛሬም ቀጥሏል።

የእምነት ልዩነት ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ባገኘባት አገራችን ''አምላክ'' አለኝ ብሎ የሚያመልኩትን ዜጎች መብት በአግባቡ አስከብሯል።በእምነት ሳቢያ የሚነሱ ጥያቄዎችም ምላሽ አግኝተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን እምነትን መሠረት ያደረጉ የሚመስሉ ችግሮች መታየት ጀምረዋል። ሃይማኖት ሰብዓዊ ፍጥረትን በተቀበለው እምነት የሚያሰባስብ ሆኖ ሳለ

*በቅርቡ እየታዘብነው ያለ ሁኔታ ግን አንዳንድ ኃይሎች የመከፋፈያና የማለያያ መሣሪያ ለማድረግ ሲሯሯጡ ማየት እየተለመደ መጥቷል።*

*በክርስትናና በእስልምና የሚንጸባረቀው የአክራሪነት አዝማሚያ ለማንምና ለምንም የማይጠቅም መሆኑን ለማመን ሩቅ ሳያስፈልግ ማየት ይቻላል።ባለፉት ዓመታት በአገራችን አንዳንድ ክፍሎች ተከስቶ የነበሩት ችግሮች ያስከተሉትን ጉዳት ማየት ብቻ ይበቃል።*

*ካለፈው ዓመት ወዲህ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ አንዳንድ አገሮች የታየውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት የሚደረገው ሙከራም የአገሪቱንና የሕዝቧን ምንነትና ታሪክ ካለማወቅ የመነጨ ነው ማለት ይቻላል።*

*እምነትን ለፖለቲካ ዓላማ ማሳኪያነት ለማዋል የሚደረገው እንቅስቃሴ ለዘመናት የዘለቀውን የትውልዶች የአብሮነት ሕይወት ለማስተጓጎል ሲጣጣር ይታያል። አፈጣጠራችን፣አስተዳደጋችንና አኗኗራችን ለአክራሪነት የሚሆን ቦታ የለውም። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተደበላልቆና ተዋህዶ ትውልዶችን የተሸጋገረው ትስስር ማንን ከማን እንደሚለይም ማወቅም ያስቸግራል።*

*በዚህች አገር በቋንቋ፣ በባህል፣ በታሪክና በሌሎች መስተጋብሮች የተሳሰረው ሕዝብ እምነቱን ለግሉ፣ የተፈጠረባት አገር ደግሞ ለጋራው አድርጎ ወራሪዎችና ድህነትን በመዋጋት ድል እያደረገባት ያለች አገር ናት። ትናንት የሃይማኖት ቀርቶ ሌሎች ችግሮች ሳይበግሩት የተነሳው ሕዝብ ዛሬ በየጊዜው የሚያጋጥሙትን ዳር ድንበሩን ወራሪዎች ከመወዋጋት ድል ለመነሳት የቻለው ተባብሮ በመንቀሳቀሱ ነው።*

*አገሪቱ እያስመዘገበች ባለችው ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ትልቁን ድርሻ እየተወጣ ያለው ሃይማኖት የለያየውና እምነቱን ከአገሩ ህልውና በላይ አግዝፎ ባነሳው ሕዝብ ሳይሆን፤ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ቆርጦ በተነሳውና ቆራጥ ሕዝብ ጉልበትና ገንዘብ ጭምር መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።ልብ ብሎ ሁኔታውን ማጤንም ይገባል።*

*መነሻው ምንም ይሁን ምን '' አንዲት አገር አንድ ሃይማኖት'' የሚል አስተሳሰብ ለማንም አይበጅም። ሲበጅም አልታየም።በምንም መስፈሪያም ይሁን በምንም መለኪያ ይህቺ አገር እንደ ብዙ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦቿ ሁሉ ቁጥራቸው ባይበዛም በውስጣቸው የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ያሏቸው ሃይማኖቶችን አቅፋ አቻችላ ትኖራለች። ዛሬ በጎዳና ሲዘዋወሩ በድንገት '' እስቲ ይህቺን እይዋት'' ተብለው የሚሰጥዎት መልዕክት የአንድ ድርጅትን ምርት ወይም አገልግሎት እንዲጠቀሙ የሚጋብዝ ብቻ አይደለም።''የእኔን እምነት ተቀላቀሉ'' የሚሉ ወገኖቻችንም ናቸው። አምነን ከተቀበልን እሰየው። አሊያም በራሳችን እምነት መጓዛችንን እንቀጥላለን። ግዳጅ የለውምና ተቻችሎና ተከባብሮ መኖርን የመሰለ ምን መልካም ነገር አለና!*

*በኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖታዊ መንግሥት ማቋቋምስ የትኛውን እምነት ጠቅሞ የትኛውን ለመጉዳት? ኸረ ለመሆኑ ማን በይ ማን ተመልካች ሊሆንስ ነው?ይህቺ አገር የሁላችንም ናት። የአንዱ እምነት ተከታዮች ባለ አገር የሌላውስ?ኢትዮጵያ የሁላችንም በመሆኗ እምነት ያላቸውንም ሆነ ኢ-አማንያን ዜጎች በማንነታቸው ኮርተው የሚኖሩባትና ሊኖሩባትም የሚገባ ናት።*

የካፒታሊስቱ ዓለም በኢኮኖሚ ቀውስና በኑሮ ውድነት፣ በአንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመታጣታቸውና በኑሮ ውድነት የሚታዩ ችግሮች እንዳሉ ይታወቃል። አለፍ ሲልም በአንድ እምነት ተከታዮች መካከል በተፈጠረ ክፍፍል ግጭት ይታያል። ታዲያ የአነዚህን አገሮች ግርግርና ትኩሳት ምኗም ባልሆነችው አገራችን '' እዚያ የነደደው እሳት እዚህም መቀጣጠል አለበት'' በሚል ዘይቤ ይህንን ኩሩና ለፍቶ አዳሪ ሕዝብ ለማለያየት መነሳት ሌላው ቢቀር ''ሃይማኖታዊ መንግሥት አራማጆች አለን በሚሉት እምነት አያስጠይቅ ይሆን?

አገራችን አሸባሪነትን በምሥራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ውስጥ በመዋጋት ግንባር ቀደም ከሚባሉት አገሮች አንዷ ነች።ሰላም በደፈረሰባቸው አገሮችም ሰላም አስከባሪ ሠራዊቷን በማሰማራት አኩሪ ታሪክ በመሥራት ላይ መሆኗ ይታወቃል። አገሪቱ ወደነዚህ ዓይነት ታላላቅ ተልዕኮዎች የገባችው ውስጧ ሰላምና ተከባብሮና ተቻችሎ የመኖር ባህል ያለው ሕዝብ ስላላት ነው።ዓለም አቀፋዊና አህራዊ ተልዕኮዎችን ከመወጣት ባሻገር።

የአገሪቱን ሕዝብ ሕይወት በማሻሻል በአጭር ጊዜ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የሚታገለው ጥቂት የእምነት መሪዎች ነን የሚሉ ግለሰቦች ሃይማኖትን ሰበብ አድርገው እየከፋፈሉትና ዜግነት እየሰጡት የሚከናወን ሥራ እንደማይሆን ግልጽ ነው።ሕዝቡ ለዚህ ዓይነት አስተሳሰብና አመለካከት ቦታም አልሰጠም። ሊሰጣቸውም አይገባም። ይሄ አጓጉል መንጠራራት ትርፉ ውድቀት እንዳይሆን ቆም ብሎ ማሰለሳሰል ይጠይቃል።

ሕዝቡ በአገሪቱ ልማትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አንድነቱን ይበልጥ እያጠናከረ ለትውልዶች የሚዘልቁ ተግባራትን እያከናወነ ታሪክ በመሥራት ላይ ነው። የአገሪቱን መልካም ገጽታ የመገንባትና የቀድሞ ገናናነቷን የመመለስ ተግባሩንም ለአፍታ የሚዘነጋ ሥራ አይደለም።

የሕዝቡን ይሁንታ ያገኘ መንግሥት በመመስረትም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ሥርዓት እውን ከሆነ እነሆ ሁለት አሥርት አልፎአል። ህዝቡም በምርጫው የሚበጀውንና የማይበጀውን እየለየ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ወደፊት እንጂ ወደኋላ የሚመለስበት አማራጭም አቋራጭም የለውም። የመጣበት ውጣውረድ በሚገባ ይገነዘባልና።

ኢትዮጵያን የዚህኛው ወይም የዚያኛው እምነት ተከታዮች ብቻ አድርጎ በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ አገርና መንግሥት የመገንባቱ ጉዳይ ቦታው እዚህ አይደለም፣ በጊዜ ቀመር ቢሰላም ፋሽኑ ያለፈበት ቅዠት ነው። የውሁዳን ውሁድ የሆኑ ሕዝቦች የሞሉባት፣ በዚህም ውሁድነታቸው የሚኮሩባት፣ ከዚያም በዓለም የተለያዩ ሃይማኖቶች ተቻችለው የሚኖሩባት ተብላ በተምሳሌነት የሚታዩባት አገር ነች።ይህም ሲያኮራን እንጂ ሲያሳፍረን አልታየም፤ የተጨባጩ ማንነታችን መገለጫ ነውና።

የአገሪቱ ሕዝብ ተሳትፎውን በልማትና መልካም አስተዳደርን ለማምጣት የሚያደርገውን ትግል እያጠናከረ ሕይወቱን እያሻሻለ ለትውልዶች ለመትረፍ ጥረቱን

ይቀጥላል። እያስመዘገበ ያለውን ውጤትም ይቀጥልበታል።ከውጤቱ በተጨባጭ ተጠቃሚ እየሆነ ነውና።

ሕዝቡን በእምነት ከፋፍሎ የራስን ድብቅ የፖለቲካ ዓላማ ለማራመድ የሚደረገው ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ መክሸፉ ላይቀር ትዝብት ውስጥ መጣሉ በራሱ የሚያስተዛዝብ ነው። '' አገር የጋራ ሃይማኖት የግል ነው'' የሚለውን ምርጥ ብሂልም ማስታወስ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ።እኛነታች ነውና።

በእምነት ስም ለዘመናት ተጋብቶና ተዋልዶ የኖረን ሕዝብ ለመለያየት የሚከናወነው ጥረት ዛሬም በፍቅርና በመግባባት ላይ የተደላደለውን ጠንካራ መሠረት ሊያናጋ አይገባውም። የዚህን ሕዝብ ታሪክ ያለማወቅና ከዚህም አለመማር ካልሆነ በስተቀር ጥያቄው በኢትዮጵያ ቦታ የለውም።

የከረረ ነገር ክረቱ ከጦዘ መበጣጠሱ አይቀርም። ሁሉም በልክ ካልሆነም እንደዚያው ነው። የከረረና ''ካለ እኔ'' የሚል አመለካከትም ለማንም ሲበጅ አልታየም።ስለዚህ ሁሉን በልኩ ማድረጉ ይጠቅማል።

የራስን እምነት ብቻ ለማስከበር የሚደረግ እንቅስቃሴ ሕገ መንግሥቱንም ይጻረራል። መጠፋፋትን በማስከተል ለሕልውናችንም ስጋት ይሆናል። በተጨባጭ እያየነው ያለ እውነታም ቀረበ ብሎ መመርመርና ተገቢውን መፍትሔ ማስቀመጥ የሚፈልግ ነው እላለሁ።

የሃይማኖት ጽንፈኝነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን የሚቆጣጠርበት ዕድል ሊኖረው ይችል ይሆናል።እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ደግሞ ነባራዊ ሁኔታው ምቹ ስላልሆነ ሊተገበር አይችልም። ጽንፈኝነት የሌሎችን መብት በመናድ ለራስ እምነት ብቻ በመቆም የሌሎች እምነት ተከታዮችንም ሆነ ኢ-አማኒ ዜጎችን መብትም ስለሚጋፋ እዚህ አያዋጣም።የአገሪቱ ዜጎች መተዳደሪያ የሆነውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በተለይም የእምነት ነጻነትን ይጻረራል።

የሃይማኖት አክራሪነት ፀረ- ልማትና ፀረ -ዴሞክራሲ አስተሳሰብን በማዘሉ በተለይ እንደ እኛ የብዙ እምነቶች እናት ለሆነች አገር የጥፋት ምንጭ ይሆናል። የአፋኝነት ባህርይ ስላለውም ሌሎች እምነታቸውን በነጻነት እንዳያራምዱ ያደርጋል። በእምነቶቹ በራሳቸው ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች ጭምር ይጋፋልና አይበጅንም።

ለአገራችን የማይጠቅመውንና ከአፈጣጠራችን ጀምሮ አብሮን ሊጓዝ የማይችለውን አጓጉል አስተሳሰብ በመዋጋት እምነታችን በነጻነት ማራመድ ይጠበቅብናል።ለመሆኑ የትኛው መጽሐፍ ይሆን ''ወንድም/እህትህን አትውደድ። እምነቱንም አክብረህለት/ሽለት አብሮህ/ሽ እንዳይኖር አድርግ/ጊ የሚለው''?

**አባቶቻችን የተውልንን የመከባበርና የመቻቻል ባህላችን በማጠናከር የህዳሴ ጉዞአችንን እንቀጥል!!!**